በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት /2016 ዓ/ም
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የ2015 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

I. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1.1 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ላልሆኑ ተሽከርካሪዎች የተከፈለ ክፍያ፤

- ከቀረቡልን የመ/ቤቱ የመኪና ዝርዝር ውስጥ ላልተገኙ 31 መኪናዎች ለኢትዮጵያ መድን ድርጅት የኢንሹራንስ ክፍያ ብር 892,452.23 አላግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- የጽ/ቤቱ የተሽከርካሪዎች ነዳጅ ክፍያ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለአዋሽ ተፋሰስ አስተዳደር ጽ/ቤት ብር 98,383.80 እና ለስምጥ ሸለቆ አስተዳደር ጽ/ቤት ብር 126,135.72 በተለያዩ የወጪ ማመሳከሪያ ቀንና ቁጥሮች

በድምሩ ብር **224,519.52** በጽ/ቤቶቹ የመኪና ዝርዝር ውስጥ ላልተካተቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ የተቀዳላቸው መሆኑ፣

1.2 በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል። በዚሁ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ ለ2015 በጀት ዓመት በየበጀት ፕሮግራሞቹ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከመደበኛ በጀት ብር 48,599,678.88 ከካፒታል በጀት ብር 565,058,313.26 ሲሆን በድምሩ ብር **613,657,992.14** ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መሆኑ መሆኑ፣

2 የሕጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Matters)፤

2.1 የህንፃ ጥገና እና የአሉምንየም አገልግሎት ግዥ በአንድ ላይ የግንባታ ዘርፍ ስራ በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በውስን ጨረታ በድምሩ ብር **65,505,288.81** ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፡

2.2 በሪፖርቱ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,274,624,339.53 ውስጥ ብር **218,363,536.17** በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.3 በሪፖርቱ ከሚታየው ተከፋይ ሂሳብ ብር 131,200,863.60 ውስጥ ብር 11,723,494.35 ያልተወራረደ መሆኑ ታውቋል፡፡

3 ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

3.1 የቋሚ እና አላቂ ዕቃ አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፤

የቋሚ ግምጃ ቤትን በሚመለከት

ሳህልተ ምህረት የሚገኘው ቅጥር ግቢ ውስጥ

- በ2015 ዓ.ም ወደ ክልሎች የሚሰራጩ ናቸው በሚል በውድ ዋጋ የተገዙ ብዛት ያላቸው የውሃ ትቦዎች፤ ብዛት ያላቸው ጌት ቫልቭ፤ የተለያየ አይነት ፓይፕ እና የፓይፕ አክሰሰሪዎች፤ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ ምንም አይነት መከለያ ሳይደረግላቸው ለፀሀይና ለዝናብ እንዲሁም ለስርቆት በሚያጋልጥ ሁኔታ ሜዳ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆናቸው፤
- ንብረት ክፍሉ ከላይ የተጠቀሱትን ንብረቶች ንብረቱን የተረከበበትም ሆነ መዝግቦ የያዘበት ሰነድ የሌለ መሆኑ፣
- የማይሰሩ ንብረቶች ከሚሰሩ ንብረቶች ጋር ተደባልቀው አንድ ላይ የተቀመጡ መሆናቸው፣
- ብዛታቸው 5 የሆኑ አገልግሎት የሰጡ ሮቶዎች ያለምንም መከለያ ለፀሀይና ለስርቆት በሚያጋልጥ መልኩ ሜዳ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆናቸው፤

አምቼ የሚገኝ ኮንስትራክሽን ቱልስ ክፍል

- ብዛታቸው 37 የሚሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ (የተበላሹ) ሶላሮች አገልግሎት ከሚሰጡት ንብረቶች ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ መሆኑ እና ይህ በባለፈው በጀት አመትም የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ገቢ የተደረገ የውሃ ማጣሪያ እስካሁን ድረስ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

- ብዛታቸው 2 የሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ (የተበላሹ) ታብሌት ኮምፕዩተሮች አገልግሎት ከሚሰጡት ንብረቶች ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ መሆኑ፣
- በሳይንቲፊክ ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለየዩ ኮምፒውተሮች እና የኮምፒውተር ተዛማጅ ዕቃዎች፣7 የውሃ ማጣሪያዎች፣ 26 ፋክስ ማሽን፣ 13 ኮፒ ማሽን 27 እስካነሮች፣ 12 ሂተሮች፣ 131 ላፕቶፖች ለብዙ አመታት በመመሪያው መሰረት መወገድ ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ አገልግሎት ላይ መዋል ሲገባቸው በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው በንብረት ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው፣
- በአጠቃላይ በአካላዊ ምልከታችን አምቼ የሚገኘው ቅጥር ግቢ ውስጥ የተለያዩ አሮጌ ጎማ፣ ቁርጥራጭ ብረቶች፣ ከኤልፓ(ከውሃና መስኖ ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር) የመጡ መኪኖች፣ በብልሽት አገልግሎት የማይሰጡ መኪኖች፣ብዛት ያላቸው ቆርቆሮዎች እና ብዛት ያላቸው የውሃ ትቦዎች በየሜዳው ተበታትነው የሚገኙ መሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ለማየት ችለናል፡፡

<u>አላቂ ግምጃ ቤትን በሚመለከት</u>

ብዛት ያላቸው የተለያየ አይነት የስቴፕለር ሽቦ መንቀያዎች፣ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቲተሮች ብዛት ያላቸው የተለያየ አይነት ፓዶች እና ብዛት ያላቸው ቢን ካርዶች የሚወገዱ በሚል ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው መቀመጣቸው በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

4 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው፡</u>

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ3-61173 ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-15269 እና መከ-012 ተሸከርካሪዎቹን ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እየተጠቀመባቸው ቢሆንም ንብረትነቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆናቸው በኦዲት ዳሰሳ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

5 የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሰርት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን

የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እርምጃ ያልተወሰደባቸው፡-

1. **<u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች በገንዘብ ደረጃ፤</u>**

<u>የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

<u>የ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤</u>

ለተለያዩ ስምንት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት ደመወዝ በጠቅላላው ብር 19,371.57 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

<u>የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤</u>

- የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ሲሄዱ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ላልሆኑ አቶ ኃይሉ አርቃ እና አቶ እሸቱ ቦልካ ለተባሉ ግለሰቦች በጠቅላላው ብር 6,242.00 የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ በኖክ ካርድ በብር 300,000.00 የነዳጅ ግዥ የፈጸመ ሲሆን፣ በማደያው ውስጥ ምንም ነዳጅ የሌለ በመሆኑ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የቀድሞ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ የሆኑትን ሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሶ የካቲት16 ቀን 2010 ዓ.ም ለጽህፈት ቤቱ የፍርድ ውሳኔ በተሰጠው መሰረት ከተከሳሹ ዋስ ላይ በየወሩ እየተቀረጠ በ2012 በጀት ዓመት ብር 10,532.96 እንዲሁም በ2013 በጀት ዓመት ብር 19,467.04 በድምሩብር 30,000.00 ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 270,000.00 ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች፤</u>

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 9 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ እንዲሁም ከጥር 13 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ በአዳማ ድሬ ኢንተርናሽናል ሆቴል ወርክሾፕ ባካሄደበት ወቅት አለአግባብ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ብር 207,467.00 ሁኔታው በውስጥ ኦዲት ክፍሉ አማካኝነት እንዲጣራ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የኦዲት ክፍሉ ሁኔታውን አጣርቶ አንደኛው ክፍያ ለውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ሁለተኛው ክፍያ ደግሞ ለአልጋ ተብሎ እንዲከፈል

የተደረገ መሆኑን ሚያዚያ 11 ቀን 2008 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት መሰረት ብር 14,943.50 ብቻ ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ብር 192,523.50 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

የ2012 በጀት ዓመት የቀድሞው ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የኦዲት ግኝቶች፤

- ጽህፈት ቤቱ በዲላ ከተማ አስተዳደር የእንቦጭ ወራሪ አረምን የመቆጣጠርና የማስወገድ ሥራ ላይ ምክክር ለማድረግ ከጥር 19 እስከ 20 ቀን 2012 ዓ.ም በተዘጋጀ ስብሰባው ለሁለት ቀናት እንዲሁም የስብሰባው ተሳታፊዎቹ ሲመጡና ሲሄዱ ለሁለት ቀናት በጠቅላላው የአራት ቀናት የውሎ የወሎ አበል ክፍያ መፈጸም ሲገባው የ7ቀን የውሎ አበል በመፈጸሙ ምክንያት አለአግባብ የተከፈለው ብር 11,169.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች የነበሩ 8 ግለሰቦች በዝውውር ምክንያት ወደ ተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን እና አዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት ሲሄዱ ይገለገሉበት የነበረውን ብር 118,302.37 ዋጋ ያላቸው ቋሚ ንብረቶችን ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር የምክክር ፎረም በሀዋሳ ከተማ ባዘጋጀበት ወቅት ለተሳታፊዎች በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር CPV 462478 የውሎ አበል ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ስብሰባው የተካሄደው ከጥቅምት 3 እስከ ጥቅምት 4 ቀን 2012 ዓ.ም ሁለት ቀን ሲመጡና ሲሄዱ በጠቅላላው የአራት ቀናት የውሎ የወሎ አበል ክፍያ መፈጸም ሲገባው የ6 ቀን የውሎ አበል በመፈጸሙ ምክንያት አለአግባብ የከፈለው ብር 8,000.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

የ2011 በጀት ዓመት የቀድሞው ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የኦዲት ግኝቶች፤

- የተፋሰስ ውሃ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በንኡስ ተፋሰስ ውስጥ ለሚገኙ ትልልቅ የውሃ ተጠቃሚዎችን የውሃ አጠቃቀም አያያዝና ብክለት ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባው የተካሄደው ጥር 17/2011 ለአንድ ቀን ቢሆንም ጽህፈት ቤቱ መፈጸም ካለበት የውሎ

አበል ክፍያ በላይ አላግባብ የከፈለው ብር 24,177.65 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ጽህፈት ቤቱ ከታህሳስ 26 እስከ 27 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር የዩኒቨርስቲ ትስስር ፎረም የምክክር መድረክ በአበበ ዘለቀ ኢንተርናሽና ሆቴል ባዘጋጀው ስልጠና ተሳታፊዎቹ የቆዩበት ሁለት ቀን ብቻ ቢሆንም ጽህፈት ቤቱ መፈጸም ካለበት በላይ አላግባብ የከፈለው ብር 47,116.50 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ ከፈጸመው የስልክ አገልግሎት ክፍያ ውስጥ ብር 10,545.74 ከኢትዮጵያ ዉጪ ለግል ጉዳይ ዩናይትድ አረብ ኢሚሬት፣ ሊባነን እና ኔዘርላንድ በተደጋጋሚ ተደወለበትና የቴክስት መልእክት ለተላከበት የተፈጸመ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ በወላይታ ሶዶ ከተማ የዩኒቨርስቲ ትስስር ፎረም የምክክር መድረክ ባዘጋጀበት ወቅት 8 ባለሙያዎች ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ መጥተው ጥናታዊ ጹሁፋቸውን ያቀረቡ ሲሆን ግለሰቦቹ ምንም እንኳ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቢያቀርቡም የንግድ ፍቃድ ስላላቀረቡ በጠቅላላው ከተፈጸመው ክፍያ ብር 28,500.00 ላይ 30% የገቢ ግብር ብር 8,550.00 መሰብሰብ ሲገባው 2% ብር 570.00 ብቻ በመሰብሰቡ ምክንያት ብር 5,880.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- ኅዳር 2 ቀን 2008 ዓ.ም የጽህፈት ቤቱ ሥራ አመራር አባላት መሥሪያ ቤቱ ለገዛቸው ሞተር ሳይክሎች የሚሰጠው ቤንዚን እንዲወሰን በቀረበው ሃሳብ መሰረት ለሞተር ሳይክል ተጠቃሚዎች በወር 15 ሊትር ቤንዚን እና 1 ሊትር ዘይት ተገዝቶ እንዲሰጥ በተወሰነው መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለሁለት ሰራተኞች የ30 ሊትር ቤንዚን እና 2 ሊትር የሞተር ዘይት መግዣ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 462368 ተከፍሎ ሂሳቡ እንዲወራረድ በመደረጉ ምክንያት ብር 1,250.70 አለአግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑ፤

- ጽህፈት ቤቱ በተፋሰስ ደረጃ የተፋሰስ እቅድ (Basin plan) ዝግጅት ላይ ሃያ ስምንት የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች እና ሁለት የአርሲ እና የወላይታ ዩኒቨርስቲ ሙሁራን ከሚያዝያ 14 ቀን 2011 እስከ ግንቦት 13 ቀን 2011 ድረስ ለሰላሳ ቀን የእቅድ ዝግጅቱ ላይ የተሳተፉ ሲሆን ለሴንትራል ሃዋሳ ሆቴል ከተፈጸመው የውሃአቅርቦትና የሪፍሬሽመንት አገልግሎት ክፍያ መረዳት ቢቻልም በአዋሳ ሴንትራል ሆቴል ስብሰባ ላይ በነበሩበት ወበተለያዩ ቦታዎች መስክ እንደነበሩ በማስመሰል ያለአግባብ የተፈጸመው ከብር 39,230.00 ውስጥ ብር 28,691.19 ተመላሽ ሆኖ ቀሪው ብር **10,538.81** የውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለመስክ ስራ በናሆም የመኪና ኪራይ ወደ ተለያየ ስፍራ የተንቀሳቀሱ መሆኑ ቢታወቅም ግለሰቦቹ ለስራ የቆዩበት ቀናትን ከመኪና ኪራይ ክፍያ ለመረዳት ቢቻልም በጠቅላላው መስክ ከቆዩበት ቀናት በላይ በብልጫ የተከፈላቸው ብር **28,269.40** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

የ2011 በጀት ዓመትበቀድሞ አባይ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የኦዲት ግኝቶች

የአባይ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት አካል በሆነው አሶሳ ቅርንጫፍ ከሰኔ 27 ቀን 2011 እስከ ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም በአለም አቀፍ ደረጃ በሰፊው በመተግበር ላይ ያለውን የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር መርሆዎች ለመተግበር የሚያስችል ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የተቀናጀ የተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት የምክክር መድረክ በአሶሳ ከተማ በብሌንዳና ሆቴል ስብሰባው የተካሄደው ከሰኔ 27 ቀን 2011 እስከ ሰኔ 28 ቀን 2011 ድረስ ለሁለት ቀን ቢሆንም ጽህፈት ቤቱ መፈጸም ካለበት የውሎ አበል ክፍያ በላይ ብር **34,952.70** ሰብሰባው ከተካሄደበት ቀን በላይና ስብሰባው ከተካሄደበት ከአሶሳ ከተማ የአበል ተመን ዉጪ አለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

የ2010 በጀት ዓመትበቀድሞ አባይ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የኦዲት ግኝቶች

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ሰራተኛ የሆኑት አቶ አንድነት ዘላለም መላኩ በ2010 በጀት ዓመት የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ላልሆኑ

4 ግለሰቦች ለምን ሥራ ጉዳይና ከየት እንደመጡ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር የውሎ አበል ክፍያ ብር 21,708.30 እንዲሁም 6 የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ደግሞ የመስክ ሥራ ሳይወጡ ለመስክ ሥራ እንደወጡ በማስመሰል ብር 3,791.30 በድምሩ ብር 55,499.60 በመሥሪያ ቤቱ በሚዘጋጀዉ የባንክ ወጪ ሰነድ እና በቀሪው ጉርድ ቼክ ላይ ግለሰቦቹ እንደወሰዱ ተደርጎ ሥማቸው የተጻፈ ቢሆንም ግለሰቡ ለፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ ተግባር በህግ አግባብ እንዲጠየቁ እና ያለአግባብ ወጪ የተደረገው ገንዘብም በአስቸኳይ እንዲመለስ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በፍርድ ውሳኔው መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

በኦዲቱ ታውቋል፡፡

<u>አባይ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የ2014 በጀት ዓመት የመ/ቤቱ ሠራተኞች ላልሆኑ ግለሰቦች የተከፈለ የውሎ አበል፤</u>

- በድምሩ ብር 17,569.20 በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የውሎ አበል የዋናው ጽ/ቤት እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኛ ላልሆኑ ሰራተኞች የተከፈለው የውሎ አበል ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በመመሪያው መሰረት ከሚፈጽመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ለግንባታ ለስራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን በመያዣ መልክ ተቀንሶ በተከፋይ በመመዝገብ ብር 12,817,269.80 መያዝ ሲገባው ያልተቀነሰ መሆኑ ከክፍያዎቹ ተቀንሶ ያልተያዙ የመያዣ ሂሳቦች ተመጣጣኝ መያዣ መ/ቤቱ መያዝ ስላለበት ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ገንዘቡ ተመላሽ ተደርጎ በመያዣነት ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2016 ዓ.ም